# ከቅንጅት የድጋፍ ድርጅት በዩናይትድ ኪንግደም የተሰጠ መግለጫ፣

የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት በዩናይትድ ኪንግደም በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተመስርቶ፣ ፍትህና ዲሞክራሲ በሐገራችን እንዲሰፍን ለሚደረገው ትግል ድጋፍ በመስጠት መንቀሳቀስ ከጀመረ እነሆ ፣ከሁለት አመታት በላይ አስቆጥሯል። በእነዚህ ሁለት አመታት ውስጥ በሐገራችን ምርጫ 97ን አስከትሎ በሕዝብ እና በሕዝብ መሪዎች ላይ የደረሰውን ግፍ በመቃወም፣ በግፍ ለተገደሉ ፍትህን፣ ለተጎዱ አስፈላጊውን ካሳ፣ የታሰሩት ደግሞ፣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ፣ በመጠየቅ ከሌሎች መሰል እህት ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ ከፈተኛ ዘመቻ አካሂዶል። ምንም እነኳን የታሰበው ሁሉ ተግባራዊ ባይሆንም፣ በተለይ የቅንጅት መሪዎችን ከእስር ቤት ለማስወጣት በተደረገው ጥረት ውስጥ፣ ድርጅታችን የራሱን አስተዋጻኦ አድርጓል የሚል እምነት አለን።

የቅንጅት መሪዎች ከእስር ከተፈቱም በኋላ በተለይ ወደ አውሮፓ  የመጣውን ልዑካን ቡድን በዩናይትድ ኪንግደምና በአውሮፓ ያደረገው ጉብኝት የተሳካ እንዲሆን፣ የድጋፍ ድርጅታችን በአስተባባሪነት የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል ።

የድጋፍ ድርጅታችን የዛሬ ሁለት አመት በፊት በዲሞክራሲያዊ መንገድ ሲመሠረት፣ በድጋፍ ድርጅቱ የመመሥረቻ ሰነድ ላይ፣ የድጋፍ ድርጅታችንን ለመመስረት የአስፈለገበት ዋና ምክንያት፣ “ቅንጅት የአንድነትና የዲሞክራሲ  ፓርቲ በሐገራችን የዲሞክራሲ ሥርአት ለመመስረት በሚያደርገው ትግል፣ ሁለ ገብ የሆነ ድጋፍ ለመስጠት”  የሚል ነው።

በእኛ እምነት በሐገራችን የዲሞክራሲያዊ ሥርአት እንዳይመሰረት ከምንምና ከማንም በላይ ተጠያቂው የወያኔ ዘረኛ አምባገነን ቡድን ነው። ይህም ሆኖ በእኛም በኩል የዲሞክራሲን መሰረታዊ እሴቶችን መቀበልና መርሆችንም መተግበር የተቸገርንባቸው ሁኔታዎች ተከስተዋል።

ይህ ሁኔታ በቅንጅት ከፍተኛ አመራር አካባቢ በታየበት ወቅት፣ የድጋፍ ድርጅታችን የመርህ አቋም በመውሰድ፣ ይህ አዝማሚያ በአጠቃላይ ትግሉ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት በማሰብ በአስቸኳይ እዲታረምና እንዲስተካከል መግለጫ በማውጣት  ጠይቋል። በዚሁም መግለጫው፣ በሐገር ቤት ዲሞክራሲያዊ መሠረት ላለው እንቅስቃሴ ድጋፉን እንደሚቀጥል ገልጿል። በተለይም  በድጋፍ ድርጅታችን ውስጥ መሰረታዊ የሆነውን  ዴሞክራሲያዊ  አሰራር መርህ ያልተከተሉ አዝማሚያዎችና ተግባራትን በጽኑ ስንታገል ቆይተናል።

በተለይ አሁን የድጋፍ ድርጅታችንን የሚመራው የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የሥራ ዘመኑን ጨርሶ፣ የአባላት ጠቅላላ ጉባዔ ጠርቶ፣ ሀላፊነቱን ለማስረከብ ዝግጅት በሚያደርግበት ወቅት፣ የድርጅቱን ዲሞክራሲያዊ አሰራር የጣሰ አካሄድ በሁለት የአመራር አባላት ላይ ታይቷል። ይህንን ሁኔታ፣ በድርጅታችን ደንብ እና ሥርአት መሠረት ማስተካከል፣ ጊዜ የሚጠይቅ ስለነበረ፣ የአባላትን አመታዊ ጉባዔ በታሰበው የጊዜ ማእቀፍ ውስጥ መጥራት አልቻልንም። ይህንንም የጉባዔ ጥሪ መዘግየት ችግር አባሎቻችን ይረዱልናል የሚል እምነት አለን።

1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk

ሆኖም፣ ጉባዔውን ለረጅም ጊዜ ማዘግየት ተገቢነት የሌለው መሆኑን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በመገንዘብ፣ የሚያስፈልገው ዝግጅት ተጠናቆ፣ ዕሁድ ሜይ 11 ቀን 2008 ዓ.ም እንዲጠራ ወስኗል። ይህ ጉባዔ የድጋፍ ድርጅታችን ወደፊት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ወሳኝነት ስላለው፣ የተሳካ እንዲሆን አባላት በሙሉ የተቻላቸውን እንዲያደርጉ ከወዲሁ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ምንም እንኳን ያለንበት ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች በሐገራችን ለዲሞክራሲ ሥርአት መመስረት የሚደረገው ትግል ትልቅ ፈተና ውስጥ መውደቁን የሚያሳይ ቢሆንም፣ የድጋፍ ድርጅታችንን በዲሞክራሲ እሴቶችና መርሆች እያጠናከርን ከሄድን፣ በሐገራችን አማራጭ የሌለውን፣ የነጻነት፣ የፍትህ፣ የአንድነት ፣ የሰላም ዋስትና የሆነውን የዴሞክራሲ ሥርአት ምስረታ እውን ለማድረግ በሚደረገው ትግል ውስጥ፣ ዛሬም እንደ ትላንትናው፣ የድጋፍ ድርጅታችን የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚችል እርግጠኞች ነን።

በሐገራችን የዴሞክራሲ ሥርአት ይገነባል!!!

የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት በዩናይትድ ኪንግደም፣
ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣
ለንደን፤
አፕሪል 2008